# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ 217206

ቀን ጥቅምት 3 2015ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡ አቶ ተስፋው ሲሳይ ሹምዬ፡- ጠበቃ ፍፁም ህይወት ቀረቡ

ተጠሪዎች፡ 1ኛ. ወ/ሮ የግሌ መንግስቴ ሀብቴ፡- ቀረቡ

2ኛ. አቶ ተሾመ ሲሳይ ሹምዬ፡- ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካች የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ በኮ.መ.ቁ 109808 በ8/2/14ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 279986 በ24/3/14ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ቅር በመሰኘት በ28/3/14ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ 1ኛ ተጠሪ በስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በ2ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት ክፍቺ በኋላ የንብረት ክፍፍል እና የልጅ ቀለብ የክስ አቤቱታ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 9 የቤ.ቁ አዲስ አዋሳኞቹ በስር ክሱ ላይ የተገለጹትን 130ካ.ሜ ላይ የሚገኝ 5 ክፍል ቤት በትዳር ወቅት ያፈራነው የጋራ ንብረታችን በመሆኑ እንድንካፈል

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የልጅ ቀለብ እና ሌሎች ንብረቶችንም በተመለከተ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ክስ የቀረበበትን ቤት ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ሸጠን ተጠቅመንበታል በማለት ተከራክረዋል፡፡ በሌሎቹ የ1ኛ ተጠሪ የዳኝነት ጥያቄዎችም ላይ መልስ አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ለጉዳዩ ተገቢ ናቸው ያላቸውን ጭብጦች ከያዘ፤ ተጠሪዎች በየራሳቸው ያቀረቧቸውን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ከሰነድ ማስረጃዎች ጋር ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪዎች የመጀመሪያውን ቤት እንደሸጡ ምስክሮቻቸው አስረድተዋል፡፡ የተሸጠውም ቤት በ150ካ.ሜ ላይ የሚገኝ 2 ክፍል እና አዋሳኞቹም ክስ ከቀረበበት ሌላ መሆኑን፤ ክርክር የቀረበበት ቤት በ130ካ.ሜ ላይ የሚገኝ 5 ክፍል ቤት እና በ2ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ መሆኑን፤ ተሸጧል የተባለው ቤት እና አሁን ክስ የቀረበበት ቤት የቦታ ስፋት አዋሳኞቻቸው እንዲሁም የቤቶች ብዛት እንደሚለያይ ማስረጃዎች ያስረዳሉ፡፡ ስለሆነም ክስ የቀረበበት ከላይ የተገለጸው ቤት የተጠሪዎች የጋራ ንብረት ነው በማለት፤ ቤቱን ተጠሪዎች እንዲካፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ሌሎች ንብረቶችንም ሆነ የልጅ ቀለብንም በተመለከተ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ከላይ በተገለጸው ክስ የቀረበበትን ቤት በተመለከተ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በሰጠው ትእዛዝ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ክስ የቀረበበትን ቤት በተመለከተ ከላይ በተሰጡት ውሳኔ እና ትእዛዝ ቅር በመሰኘት ሲሆን ይዘቱም 1ኛ ተጠሪ ባለቤታቸው ከነበሩት 2ኛ ተጠሪ ጋር በትዳር ውስጥ አፈራን ያሉት በአዲስ አበባ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 9 የቤ.ቁ አዲስ የሆነው አዋሳኙ በስር ክሱ ውስጥ የተጠቀሱትን 130ካ.ሜ ይዞታ ስፋት ያለው 5 ክፍል ሰነድ አልባ ሰርቪስ ቤት ተብሎ የቀረበውና የወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት በቦታው ተገኝቶ ለክቶ ለፍ/ቤቱ መልስ የሰጠበት አመልካች ሰነድ አልባ መኖሪያ ቤት በሰሜን ጀማነህ ታችበሌ፤ በደቡብ አለም አሊ፤ በምስራቅ አቶ ጀማነህ ታችበሌ፤ በምዕራብ መንገድ የሚያዋስነውን ሰነድ አልባ መኖሪያ ቤት እንደማይገናኝ አመልካች የጣልቃገብ አቤቱታ አቅርቤ እያለ የስር ፍ/ቤቱም ለአቤቱታዬ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ትእዛዝ ከሰጠ በኋላ በክርክሩ ሳያሳትፈኝ የተጠሪዎችን ምስክሮች ብቻ በመስማት ውሳኔ መስጠቱና የከፍተኛ ፍ/ቤቱም የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ማጽናቱ በክርክሩ ተሳታፊ እንዳልሆን በመገደብ የአመልካች መብት የሚጎዳና ፍትህ የማግኘት መብቴን የሚጻረር መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ትእዛዝ እንዲሻር እና አመልካች ባቀረብኩት የጣልቃገብነት አቤቱታ ማስረጃ መሰረት ውሳኔ እንዲሰጥልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ አቤቱታቸው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ በስር ፍ/ቤት አመልካች ወደ ክርክሩ እንዲገባ ብይን ተሰጥቶ ባለበት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ስለአከራካሪው ቤትን በተመለከተ ከአመልካች አንጻር ምንም ሳይል ፍርድ መስጠቱ ስነስርአት ህጉን የተከተለ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ3/5/14ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎ 1ኛ ተጠሪ በ26/5/14ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ

አመልካች በስር ፍ/ቤት በጣልቃገብነት ገብቶ ለመከራከር ያመለከቱ ሲሆን ፍ/ቤቱም በስነስርአቱ መሰረት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በማድረግና ጉዳዩን በመመርመር አመልካች ጣልቃ ገብተው የሚከራከሩበት መሰረት የሌለ በመሆኑ ጥያቄያቸውን ከጅምሩ ውድቅ በማድረግ በተጠሪዎች መካከል የነበረውን ክርክር በማስቀጠል የሰጠው ውሳኔ እና ይህንኑ ውሳኔ ከፍተኛ ፍ/ቤት ማጽናቱ ስህተት የሌለው በመሆኑ እንዲጸና፤ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈለኝ እንዲወሰንልኝ ብለዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በ26/5/14ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት ቢወሰንላቸው እንደማይቃወሙ ገልጸዋል፡፡

አመልካች በ11/6/14ዓ.ም በተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር የፍ/ቤቶች በአዲስ አበባ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 9 የቤ.ቁ አዲስ የሆነው አዋሳኙ በስር ክሱ ውስጥ የተጠቀሱትን 130ካ.ሜ ይዞታ ስፋት ያለው 5 ክፍል ሰነድ አልባ ሰርቪስ ቤትን በተመለከተ የሰጡት ውሳኔ እና ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 41(1) ባንድ ክስ ሌሎች ተከራካሪ ወገኖች በክርክር ላይ ባሉበት ግዜ ማናቸውም ሶስተኛ ወገን በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ሲሆን ከፍርድ ውሳኔ በፊት ጣልቃገብ ሆኖ ለመከራከር እንደሚችል ደንግጓል፡፡ የዚህ ህግ ቁጥር 41(3) የጣልቃገብነቱ መብት ተወስኖ አመልካቹ በክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን የተፈቀደ እንደሆነ የጣልቃገቡ ማመልከቻ ግልባጭ ለተከራካሪዎቹ ወገኖች እስኪሰጣቸው ድረስ ክርክሩ ታግዶ እንደሚቆይ ደንግጓል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ እንዲረዳ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ የኮ.መ.ቁ 109808 የሆነውን መዝገብ በትእዛዝ አስቀርቦ እንደመረመረው በተጠሪዎች መካከል ከፍቺ በኋላ የንብረት ክርክር እየተደረገ ባለበት ወቅት አመልካች በ9/7/13ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት አቤቱታ ተጠሪዎች እየተከራከሩበት የነበረውን በአዲስ አበባ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 9 የቤ.ቁ አዲስ የሆነው አዋሳኙ በስር ክሱ ውስጥ የተጠቀሱትን 130ካ.ሜ ይዞታ ስፋት ያለው 5 ክፍል ሰነድ አልባ ሰርቪስ ቤት በመንደር ውል ከአቶ ጀማነህ ታችበሌ እና ከወ/ሮ አስናቁ ታደሰ በ2004ዓ.ም የገዛሁት ቤት ነው በማለት ጣልቃገብተው እንዲከራከሩ እንዲፈቀድላቸው አመልክተው ፍ/ቤቱም በአቤቱታው ላይ የተጠሪዎችን አስተያየት ከተቀበለ በኋላ አቤቱታውን መርምሮ በ7/8/13ዓ.ም አመልካች በክርክሩ ጣልቃገብተው እንዲከራከሩ ብይን የሰጠ መሆኑን ከመዝገቡ ተገንዝቧል፡፡

ሆኖም የስር የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች ተጠሪዎች ከላይ የተገለጸውን ቤት በተመለከተ እያደረጉ ባለው ክርክር ላይ ጣልቃገብተው እንዲከራከሩ በ7/8/13ዓ.ም ብይን ከሰጠ በኋላ አመልካችን የክርክሩ ተካፋይ በማድረግ ከላይ በተጠቀሰው የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 41(3) መሰረት ቤቱን በተመለከተ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን የክስ አቤቱታ እና የ2ኛ ተጠሪን መልስ ለአመልካች እንዲደርስ በማድረግ አመልካች የጣልቃገብነት ክርክራቸውን

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በጽሁፍ እንዲያቀርቡ በማድረግ እና ከዚህ በኋላም ተገቢዎቹን ህጋዊ ሂደቶች ሁሉ በመከተል በቤቱ ላይ የአመልካች መብት ምንድን ነው የሚለውንም ነጥብ ጭምር በመመርመር ቤቱን በተመለከተ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ ሊሰጥ ሲገባ አመልካችን ወደ ክርክሩ ጣልቃገብተው እንዲከራከሩ ከፈቀደ በኋላ በክርክሩ በየትኛውም ደረጃ አመልካችን የክርክሩ ተሳታፊ ሳያደርግ በተጠሪዎች መካከል ብቻ የነበረውን ክርክር በማስቀጠል ጉዳዩን መርምሮ ቤቱ የተጠሪዎች የጋራ ሀብት ነው፤ይካፈሉ በማለት ውሳኔ መስጠቱን ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት ከመዝገቡ ተገንዝቧል፡፡ በዚህ መልኩ ቤቱን በተመለከተ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ እና በዚሁ ውሳኔ ላይ የቀረበውን ይግባኝ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመሰረዝ የሰጠውን ትእዛዝ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

1. በአዲስ አበባ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 9 የቤ.ቁ አዲስ የሆነው አዋሳኙ በስር ክሱ ውስጥ የተጠቀሱትን 130ካ.ሜ ይዞታ ስፋት ያለው 5 ክፍል ሰነድ አልባ ሰርቪስ ቤትን በተመለከተ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ በኮ.መ.ቁ 109808 በ8/2/14ዓ.ም የተጠሪዎች የጋራ ሀብት ነው ፤ ይካፈሉ በማለት የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም በዚሁ ላይ የቀረበውን ይግባኝ የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 279986 በ24/3/14ዓ.ም በመሰረዝ የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ በኮ.መ.ቁ 109808 በአዲስ አበባ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 9 የቤ.ቁ አዲስ የሆነው አዋሳኙ በስር ክሱ ውስጥ የተጠቀሱትን 130ካ.ሜ ይዞታ ስፋት ያለው 5 ክፍል ሰነድ አልባ ሰርቪስ ቤትን በተመለከተ በተጠሪዎች መካከል በነበረው ክርክር አመልካች ጣልቃገብተው እንዲከራከሩ በ7/8/13ዓ.ም ብይን ከሰጠ በኋላ አመልካችን የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 41(3) በደነገገው መሰረት ቤቱን በተመለከተ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን የክስ አቤቱታ እና የ2ኛ ተጠሪን መልስ ለአመልካች እንዲደርስ በማድረግ አመልካች የጣልቃገብነት ክርክራቸውን በጽሁፍ እንዲያቀርቡ በማድረግ እና ከዚህ በኋላም ተገቢዎቹን ህጋዊ ሂደቶች ሁሉ በመከተል በቤቱ ላይ የአመልካች መብት ምንድን ነው የሚለውንም ጭምር በመመርመር ቤቱን በተመለከተ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ ሊሰጥ ሲገባ አመልካችን በክርክሩ ሳያሳትፍ በተጠሪዎች ብቻ መካከል ቤቱን በተመለከተ ክርክሩን በማስቀጠል ቤቱ የተጠሪዎች የጋራ ሀብት ነው፤ ይካፈሉ በማለት በ8/2/14ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና በዚሁ ላይ የቀረበውንም ይግባኝ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 279986 በ24/3/14ዓ.ም በመሰረዝ የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ወስኗል፡፡
3. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ የኮ.መ.ቁ 109808 የሆነውን መዝገብ አንቀሳቅሶ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 41(3) በደነገገው መሰረት በአዲስ አበባ ቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 9 የቤ.ቁ አዲስ የሆነው አዋሳኙ በስር ክሱ ውስጥ የተጠቀሱትን 130ካ.ሜ ይዞታ ስፋት ያለው 5 ክፍል ሰነድ አልባ ሰርቪስ ቤትን በተመለከተ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን የክስ አቤቱታ እና የ2ኛ ተጠሪን መልስ ለአመልካች እንዲደርስ በማድረግ አመልካች የጣልቃገብነት ክርክራቸውን በጽሁፍ እንዲያቀርቡ በማድረግ እና

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ከዚህ በኂላም ተገቢዎቹን ህጋዊ ሂደቶች ሁሉ በመከተል በቤቱ ላይ የአመልካች መብት ምንድን ነው የሚለውንም ጭምር በመመርመር ቤቱን በተመለከተ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት መልሰንለታል፡፡

4. ከላይ በውሳኔው ክፍል ተራ ቁጥር 1፤2 እና 3 ላይ ከተገለጹት ጉዳዮች ውጪ የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ በኮ.መ.ቁ 109808 በ8/2/14ዓ.ም በሌሎች ጉዳዮች ላይ የሰጠው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
5. በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
7. በዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ትእዛዝ የቀረበው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ የኮ.መ.ቁ 109808 የሆነው መዝገብ በመጣበት አኳኋን ለፍ/ቤቱ ይመለስ፡፡
8. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም